# *የጅምላ እስራት ዘመቻው ኣመፅ እንዲፋፋም ይገፋፋል እንጂ ህዝብን ኢያንበረክክም*

*(ከኦነግ ኢንፎ ዴስክ)*

ኣምባገነን መንግስታት የህዝብን ድምፅ ለማፋን እንደ መሳሪያ ከሚጠቀሙባቸው እርምጃዎች መካከል ኣንዱ የጅምላ እስራት ነው። የህዝብ ኣንገዛም ባይነት ኣመፅ እየበረታባቸው በመጣ ልክ ዜጎችን በጅምላ ኣፍሰው ማሰር የጋራ ባህላቸው ነው። እናስተዳድረዋለን ከሚሉት ህዝብ ኣመኔታ ስለሌላቸው በትንሽ ኮሽታ ተደናብረው የማስፈራራት እርምጃ ወደ መውሰድ ይገባሉ። የገዛ ጥላቸውን ይጠራጠራሉ። የህዝቦችን ሃሳብ ለመስማት ፍላጎቱም ሆነ ትእግስት የላቸውም። የህወሃት መንግስትም ኣምባገነን ስርኣት እንደመሆኑ መጠን በመሰል ባህሪያት ይገለፃል። በሃይል ከሚያስተዳድራቸው ህዝቦች ከፍተኛ ፍራቻ ስላለው በጅምላ እስራት ኣስፈራርቶና ኣፍኖ መቀጠሉን እንደ ኣማራጭ ተያይዞታል።

ባሁኑ ጊዜ ኦሮምያ ውስጥ በስፋት የሚስተዋለው ተጨባጭ እውነታም ይሄው ነው። በኦሮምያ በተለያዩ ዞኖች የተስፋፋው የጅምላ እስራት ዋነኛ ምክንያትም ምን እንደሆነ ግልፅ ነው። የህዝብ ኣመፅ ኣድማሱ እየሰፋ በመሄዱ ነው። የተማሪዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የኣርሶ ኣደሮችና የሌሎችም የህብረተሰቡ ክፍሎች ኣመፅ ወያኔን ማጣደፍ ይዞኣል። በዚህ መልኩ ኣጣብቂኝ ውስጥ የገባው ስርኣት ህዝብን በጅምላ ኣፍሶ ማሰርን ነፍሱን እንደ ማዳን እርምጃ የወሰደ ይመስላል።

ዛሬ በኦሮምያ ከዚህ የጅምላ እስራት ነፃ የሆነ ኣካባቢ ኣይታይም ማለቱ ይቀላል። ኦሮምያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምእራብ እስከ ምስራቅ ወከባ የነገሰባት ምድር ሆናለች። በተለይም ከወደ ምእራብ ኦሮምያ የሚወጡ ሪፖርቶች እንደሚያስረዱት በተለያዩ የኣካባቢው ወረዳዎች የእስራቱ ዘመቻ እየተጠናከረ በሄደ ልክ የህዝቡ ኣልገዛም ባይነት ኣመፅም እየተጫረ በመቀጣጠል ላይ ይገኛል። ከማእከላዊ ኦሮምያ የሚወጡ ሪፖርቶችም በኣካባቢው መሰል ሁኔታዎች እየተጠናከሩ በመሄድ ላይ መሆናቸውን ያስረዳሉ። በተቀሩት የኦሮምያ ኣካባቢዎችም ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ዜጎች በየእለቱ ታፍሰው እየታሰሩ መሆኑን ተጨማሪ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በጅምላ ታፍሰው የሚታሰሩት የኦሮሞ ተወላጆች ምንም ኣይነት ወንጀል የፈፀሙ ባለመሆናቸው ለይስሙላም ቢሆን ፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ የተደረጉ ይመስላል። ፍርድ ቤት ከቀረቡ ወንጀላቸው ምን እንደሆነ ስለሚጠየቅ በስመ ኣቃቤ ህግነት የተሰየሙ የወያኔ ካድሬዎች በቂ ምላሽ ኣይኖራቸውም። እናም ኣሳሪዎቹ ካድሬዎች ኣፍነው እስር ቤት ያጎሯቸውን ንፁሃን የኦሮሞ ዜጎችን እንዳፈኗቸው ቀጥለዋል። ፍርድ ፊት እንዲያቀርቧቸው የሚያስገድድ ሁኔታ ከተፈጠረም ኣስቀድመው እንዳመላቸው የሃሰት ምስክሮችና ማስረጃዎችን በማቀናጀት በንፁሃን የኦሮሞ ዜጎች ላይ የሞትና የእድሜ ልክ እስራት ብይን ማሳለፍ የተለመደ ነገር ነው። እስከ ዛሬ ድረስ በኦሮምያ የሚታየው እውነታም ይህን ኣባባል የሚያጠናክር ነው።

እውነተኛ ብሄርተኛነት የሚሰማቸውና የህዝባቸው መበደል የሚያሳስባቸው ዜጎች ሁሉ የኦነግ ኣባል ወይም ደጋፊ እየተባሉ በኣሸባሪነት ወንጀል ይከሰሳሉ። ሃገር ቤት በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱት የኦሮሞ ፖለቲካ ድርጅቶች ኣባላትም ከበስተጀርባቸው ያለው ኦነግ ነው እየተባሉ ያለፍርድ በእስራት እየተጎሳቆሉ ናቸው። እንደነ ኣቶ ኦልባና ሌሊሳና ኣቶ በቀለ ገርባ ያሉት የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ኣመራር ኣባላትም በዚሁ ውስጥ ይጠቀሳሉ። እነዚህ የኦሮሞ ዜጎች በሃሰት ውንጀላ ተይዘው ከታሰሩ በርካታ ወሮች የተቆጠሩ ቢሆንም ጉዳያቸው ከምን እንደደረሰ እስካሁን የሚተንፍስ ኣካል ኣይታይም። ከነሱ በሁዋላ የታሰሩ የሌሎች ፓርቲዎች ኣመራር ኣባላት የፍርድ ጉዳይ ለይስሙላም ቢሆን በተደጋጋሚ ሲነሳ የኦሮሞ ተወላጆቹ ጉዳይ ግን እንደተዳፈነ ቀጥሏል። የወያኔው ስርኣት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተለየ ኣደገኛ የጠላትነት ፖሊሲ የሚከተል መሆኑን ከሚያስረዱ ኣብነቶች መካከል ይሄኛው ኣንዱ ነው።

ሌላው የሚገርመውና የሚያሳዝነው ደግሞ በኢትዮጵያ ስር ስለሰደደው የዜጎች እስራት ሁኔታ ሚዛናዊ ዘገባ ያቀርባሉ ተብለው የሚጠበቁ ኣንዳንድ ነፃ ሚድያ የሚባሉ የውጭ መገናኛ ብዙሃን የሃገሪቷን እስር ቤቶች ስላጨናነቁት የኦሮሞ ዜጎች ሰቆቃና ለፍርድ ያለመቅረብ ጉዳይ ከመተንፈስ ሲቆጠቡ ይታያሉ። በዘጋቢነት ስራ ሽገር የተቀመጡ የነዚህ የውጭ ሚድያ ጋዜጠኞች የኦሮሞ ህዝብን እሮሮ በማፋን ዘመቻ ላይ ለወያኔ ደቦ የወጡ እስኪመስሉ ድረስ መተባበራቸው በርግጥ የሚያሳዝን ነው። ግፍ ሞልቶ በፈሰሰባት ኦሮምያ እምብርት ላይ ተቀምጠው ምንም ነገር ሳይተነፍሱ እንደ ኣምነስቲ ኢንተርናሺናል ያሉ ኣለም ኣቀፍ እውቅ የሰብኣዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ለኦሮምያው የጅምላ እስራት ዘመቻ ኣፅእኖት ሰጥተው መዘገባቸው እውነታውን ይበልጥ ያጎላዋል። ኣምነስቲ ኢንተርናሺናል ሰሞኑን ባወጣው ዘገባው በቅርብ ጊዜ በተካሄደ የምጅላ እስራት ዘመቻ ብቻ ከኦሮምያ ክልል በመቶ ቤት የሚሰሉ የኦሮሞ ዜጎች ታፍሰው መታሰራቸውን ኣስምሮበታል። ይህ የኣምነስቲ ዘገባ ዛሬ በኦሮምያ ውስጥ የሚታየው የወከባና የእስራት ዘመቻው ኣድማስ ከየትኛውም የሃገሪቷ ክልሎች በከፋ ደረጃ ላይ መሆኑን የሚመሰክር ነው።

ያም ሆነ ይህ የጠላት የጥቃት በትር የቱን ያህል ቢበረታም የኦሮሞ ህዝብ የተያያዘውን የበቃኝ ኣልገዛም ትግል ሊቀለብስ ኣይችልም። ተወደደም ተጠላም ዛሬ ኦሮምያ ከየትኛውም የሃገሪቷ ክልሎች በላቀ መልኩ ህዝባዊ የፀረ ወያኔ ትግሉ ተፋፍሞ የሚታይበትና ጠላትን ስጋት ውስጥ የጣለ ዋነኛው ክልል ነው። ኦሮሞ ለጠላት ኣፈና ስልቶች ኣልተበገረም። በተቻለለት መንገድ ሁሉ እምቢታውን በማሳየት ከጠላት ጋር ሆድና ጀርባ መሆኑን እያስመሰከረ ነው። ለዚህም ኣንድ ጉልህ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው ከየትኛውም ክልል በተባባሰ መልኩ በኦሮምያ ስር የሰደደው ይሄው የጅምላ እስራት ዘመቻ ነው። የእስራት ዘመቻው የተባባሰበት ኣካባቢ ማለት የኣንገዛም ባይነት ኣመፅ ወደ ኣሳሳቢ ደረጃ የተሸጋገረበት ኣካባቢ መሆኑን ይመሰክራል።

በተለያዩ የትምህርት ተቋዋማት የሚማረው ቄሮው የኦሮሞ ወጣት ከምስራቅ ምእራብ፣ ከሰሜን ደቡብ ያለው ርቀት ሳይገድበው የሚያካሄደውን ንቅናቄ ኣቀናጅቶ በጋራ እየተራመደ ነው። ቄሮው ወጣት በዘመኑ የመገናኛ ተክኖሎጂ

መሳሪያዎች በሚገባ በመጠቀም ንቅናቄውን ይበልጥ በማቀላጠፍ ወያኔን እንቅልፍ ወደመንሳት ደረጃ እየተሸጋገረ ነው። ሰፊው የኦሮሞ ህዝብም በተቻለለት ኣቅም ሁሉ ከልጆቹ ጎን ተሰልፎ ለመታገል በከፍተኛ ሞራል ተዘጋጅቷል። ይህ የኦሮሞ ህዝብ ቆራጥ የትግል ውሳኔ ነው ወያኔ ላይ ሽብር እየለቀቀ የሚገኘው።

በጥቅሉ ሲታይ የወያኔ መንግስት ዛሬ በኦሮምያ የሚያካሄደው የእስራትና የወከባ ተግባር የኦሮሞ ህዝብንና ስርኣቱን የሚያስታርቅ ሳይሆን በይበልጥ ለወሳኙ ፊልሚያ እንዲዘጋጅ የሚያስገድደው ነው። ኦሮሞ ከየትኛውም የሃገሪቷ ዜጋ በበለጠ ከቀዬው ላይ እየተፈናቀለ ነው። ለም መሬቱን እየተነጠቀ ይገኛል። ወንዞቹና ሃይቆቹ እየተበከሉበት ናቸው። ባጭሩ የህዝቡ የወደፊት ተስፋና እድል እንዲጨልም ስልታዊ ዘመቻ ተከፍቶበታል። በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቹ እየታፈሱ ይታሰራሉ። ከዚህ ወከባ ሸሽተው ወደ ጎሮቤት ሃገር የሚወጡም በደረሱበት ሃገር የስደተኛነት መብት ተነፍገው እንደ ድኩላ ይታደናሉ። የወያኔ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተያያዘው የጥቃት ዘመቻ በዚህ ብቻ ተነግሮ የሚያበቃም ኣይደለም። እነዚህ ሁሉ የግፍ እርምጃዎች ኣንድ ላይ ሲደመሩ ውጤቱ ለወያኔ የከፋ ነው የሚሆነው። የተጀመረው የኣልገዛም ባይነት ኣመፅ ይበልጥ ተፋፍሞ የስርኣቱን ፍፃሜ ያፋጥናል እንጂ የኦሮሞ ህዝብን ከቶ ማንበርከክ ኣይችልምና!

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ